# የአማርኛ ትምህርት የፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ክፍል ስድስት

1. ከሚከተሉት አንዱ አማርኛ ቋንቋ ከግዕዝ የተዋሰው ነው

ሀ) ዳርቻ ለ) አጣና ሐ) ሳይሳሳ መ) ህላዌ

2. ከሚከተሉት የቋምቋ ክሂሎች መካከል መል ዕክት ማስተላለፊያ የሆኑት የትኞቹ ናቸው ?

ሀ) ማንበብና መፃፍ ለ) መናገርና መፃፍ

ሐ) ማዳመጥና ማንበብ መ) ማዳመጥና መናገር

3. **አመዴ ቡን** አለ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ) ወዝ አጣሁ ለ) ደከመኝ ሐ) የምሄድበት አጣሁ መ) ደነገጥኩ

4. **በመንገዶቻቸው** በዚህ ቃል ውስጥ ስንት ም ዕላዶች አሉ?

ሀ) አምስት ለ) አራት ሐ) ሶስት መ) ሁለት

5. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ሁለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር አነስታይ ፆታ የተነገረ ነው።

ሀ) አመራ ለ) አመራህ ሐ) አመራሽ መ) አመራችሁ

6. ከሚከተሉት መካከል ትክክል የተተነተነው የቱ ነው?

ሀ) ስር-ሰር ለ) ስርኣ-ስር ሐ) ስር-ኣ-ስር መ) ስራ--ስር

7. እስቴር **በአፏ ሰው አትነካም** ። የተሰመረበት ሀረግ ትርጉም

ሀ) ሰው አትበላም ለ) መናገር አትችልም

ሐ) ሀሜተኛ ናት መ) ሀሜተኛ አይደለችም

8. **ማንባራም** ለሚለው ቃል ፍቺ የሚሆነው

ሀ) ኮስታራ ለ) እድለኛ ሐ) ፀጉሩ ገባ ያለ መ) መልከኛ የሆነ

9. ሰርገኛ መጣ......................

ሀ) እንቀበለው ለ) ሞቅ ሞቅ እናድርገው

ሐ) በርበሬ ቀንጥሱ መ) ቤቱ ደመቅ አለ

10. **አንበሳ** የሚለው ቃል ወደብዙ ሲቀየር

ሀ) አንበሶች ለ) አናብስት ሐ) አንበሲት መ) ሀ እና ለ

LIVEWORKSHEETS

11. ልጅቱ በትምህርቷ **ንብ ናት** ። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ፣

ሀ) ወሬኛ ለ) ጎበዝ ሐ) አውሬ መ) ሥላም የሌላት

12. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በተቃራኒ ስልት ያልቀረበው የትኛው ነው ?

ሀ) ጥሬ ከብስል ለ) ጎበዝና ሰነፍ ሐ) ላይ እና ታች መ) በላይ በላዩ

13. ጎበዝ ተማሪ በርትቶ ያጠናል። ይህ አረፍተ ነገር የተነገረበት ስልት የቱ ነው ?

ሀ) ጥያቄያዊ ለ) ትዕዛዛዊ ሐ) ሀተታዊ መ) አጋኖኝ

14. **ቆርጦ ቀጥል** ለሚለው ቃል ፍቺ ምን ይሆናል?

ሀ) ልብስ ሰፊ ለ) ውሸታም ሐ) ሃይለኛ መ) ወላዋይ

15. **የቤት ስራችሁን በአግባቡ ስርታችሁ ኑ!** ይህ አረፍተ ነገር የተነገረበት ስልት፤

ሀ) ጥያቄያዊ ለ) ትዕዛዛዊ ሐ) ሀተታዊ መ) አጋኖኝ

16. ሳል ይዞ ስርቆት......................

ሀ) ያስጨንቃል ለ) ቂም ይዞ ፀሎት

ሐ) ያስቸግራል መ) ሀ እና ለ

17. **እሰይ! ልጄ በጥሩ ውጤት ተመረቀልኝ**። ይህ አረፍተ ነገር የተነገረበት ስልት፤

ሀ) ጥያቄያዊ ለ) ትዕዛዛዊ ሐ) ሀተታዊ መ) አጋኖኝ

18. አንድ ሰው ከባድ ሀዘን እነደገጠመው ለመግለጽ ከሚከተሉት የትኛውን እንጠቀማለን?

ሀ) ፊቱን አዞረ ለ) ፊቱን ተቀባ ሐ) ፊቱን ነጨ መ) አንገቱን ሰበረ

19. አንድን ድርሰት ከመፃፋችን በፊት አስቀድመን መረጃን የማደራጀት መርህ የትኛው ነው ?

ሀ) ዘገባ ለ) አስተዋፃዖ ሐ) ማስታወሻ መ) መመሪያ

20. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ጥምር ቃል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ) ቤተመቅደስ ለ) ልብወለድ ሐ) ትልቅ ሰው መ) አየር ወለድ

21. ልጅቱ **የደም ገንቦ** ናት ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ

ሀ) ገንቦ ተሸከምአለች ለ) ቀይ ነች ሐ) የደስ ደስ አላት መ) አታምርም

LIVEWORKSHEETS

22. የቆጡን አወርድ ብላ......................

ሀ) የብብቷ ወደቀባት
ለ) ወድቃ ተሰበረች
ሐ) በጣም ተንጠራራች
መ) የብብቷን ጣለች

23. ቀያይ ፍየል መጡ። የዚህ አረፍተ ነገር ስህተት ምንድን ነው?

ሀ) የቁጥር ስህተት
ለ) የፆታ ስህተት
ሐ) የመደብ ስህተት
መ) የጊዜ ስህተት

24. አዛኝ **ቅቤ አንጓች** ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ ሊሆን የሚችለው፡

ሀ) ተላላኪ
ለ) አዛኝ
ሐ) ቅቤ ሻጭ
መ) አወደድ ባይ

25. የእንጀራ ምጣዱ **ጨበረረች** ሲል ፡

ሀ) ድቅቅ ብላ ተሰበረች
ለ) ሰማች
ሐ) ተሟሸች
መ) ቀላች

26. የውሻ ቁስል ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ የሚሆነው

ሀ) ቂም የማይይዝ
ለ) ነገር ቶሎ የሚተው
ሐ) ሀይለኛ
መ) ሀ እና ለ

ለሀይለኛ ሴት ለምትቆጣ፣
ምነው መካሪ ባል ታጣ

27. የዚህ ቅኔ ሀብረ ቃሉ ማን ነው ?

ሀ) መካሪ
ለ) ባል
ሐ) ታጣ
መ) ባል ታጣ

28. የዚህ ቅኔ ወርቁ ምንደን ነው ?

ሀ) ምነው የሚመከር በተገኘ
ለ) ምነው የምታገባው ባል ጠፋ
ሐ) ምነው የሚመከራት ባል ጠፋ
መ) ሁሉም

29. "ምናባዊ" ምን ማለት ነው?

ሀ. ፈጠራ
ለ. ህመም
ሐ. ቃላዊ
መ. ሁሉም

30. የአጭር ልቦለድ ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ኃይለ ቃል
ለ. ጥድፊያ
ሐ. ቁጥብነት
መ. ነጠላ ውጤት

LIVEWORKSHEETS

31. አካሄዱን አይተህ.........................................

ሀ) ጭብጦውን ቀማው

ለ) ቤቱን ተመልከተው

ሐ) ማንነቱን ለየው

መ) ስራውን ታውቃለህ

32. ባለቤቷን የተማመነች በግ..................................

ሀ) ቶሎ አትገባም

ለ) ለጥ ብላ ታድራለች

ሐ) ላቷን ውጭ ታሳድራለች

መ) ለ እና ሐ

33. ጆሮ ለባለቤቱ. ......................................

ሀ) አይከብድም

ለ) ባዳ ነው

ሐ) ቶሎ አያዳምጥም

መ) ጌጥ ነው

34. የወደቀ ዛፍ.........................................

ሀ) ምሳር ይበዛበታል

ለ) መቆረጡ አይቀርም

ሐ) ወሳጁ ብዙ ነው

መ) ይበሰብሳል

35. የነ ቶሎ ቶሎ ቤት................................

ሀ) መኖሪያው እሩቅ ነው

ለ) መውጫው ጠባብ ነው

ሐ) ቶሎ ይፈርሳል

መ) ግድግዳው ሰንበሌጥ

LIVEWORKSHEETS